**የጤናና ማህበራዊ አገልግሎት መምሪያ የህፃናትና ቤተሰብ አስተዳደር**
**የስደተኞች መልሶ ማቋቋሚያ ጽ/ ቤት**

**<u>በስደተኞች መልሶ ማቋቋሚያ ጽ/ ቤት</u>**
**<u>ለፖለቲካ ጥገኞች የሚደረጉ የድጋፍ አገልግሎቶች</u>**

**የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች እነማን ናቸው?**

በዩናይትድ ስቴትስ የፖለቲካ ጥገኝነት የተፈቀድልዎ ከሆኑ የስድተኞች ማቋቋሚያ ጽ/ ቤት የሚሰጣቸው አገልግሎቶችና ድጋፎች ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ የስደተኞች መልሶ ማቋቋሚያ ጽ/ ቤት ለስደተኞች ለፖለቲካ ጥገኝነት በልዩ ሁኔታ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ለገቡ የህብረተሰብ ክፍሎች ዩናይትድ ስቴትስ ንሮዋቸውን እንደገና እንዲጀምሩና እንዲቋቋሙ የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን ያስተዳድራል በባጀትም ይደግፋል ፕሮግራሙ ለተጠቃሚዎች የገንዘብ ድጋፍ፣ የጤና ኢንሹራንስ፣ የሥራ ማፈላለግ ትብብር፣ ስራ የማስቀጠር አገልግሎትና የእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት ሥልጠና አገልግሎቶች ይሰጣል::

**የመልሶ ማቋቋሚያ ፕርግራሞች በማን ይከናወናሉ?**

የመልሶ ማቋቋሚያ ፕርግራሞቹ በመንግስትና በግል ድርጅቶች በመላው ዩናይትድ ስቴተስ የሚካሄዱ ሲሆን እያንዳንዱ ክልል (State) መንግስት የተለያዩ ፕሮግራሞችን ያስተዳድራል:: በአካባቢው የሚሰሩ ድርጅቶች የትኞቹ እንደሆኑና ምን ዓይነት አገልግሎትች እንደሚሰጡ ለማወቅ ከፈለጉ በሚከተለው የስልክ ቁጥር ይደውሉ::

# 1-800-354-0365

በተጨማሪም የሚከተለውን ድረ-ገፃችንን በመጐብኘት አስፈላጊውን መረጃ ሊያገኙ ይችላሉ::
www.acf.dhhs.gov/programs/orr

**አገልግሎቱ ለተጠቃሚዎች ለምን ያህል ጊዜ ይሰጣል**

ለተጠቃሚዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች ድጋፎች ለተወሰነ ጊዜ ሊሆን ይችላል::
ፖለቲካ ጥገኝነት ከተፈቀደላቸው ቀን ጀምሮ ለስምንት ወራት የገንዘብና የህክምና እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ:: እነኝህን አገላገሎቶች ወደሚሰጡ ተቋሞች ሲሄዱ የፖለቲካ ጥገኝነተ የተፈቀደልዎት መሆኑንና መቼ እንደተፈቀደልዎ የሚያረጋግጥ ደበዳቤ ይዘው መሄድ ይጠበቅብዎታል በተጨማርም ሌሎች መመዘኛዎች እንዲያሟሉ ሊጠየቁ ይችላሉ ተጨማሪ መመዘኛዎች ወደ ተቋማቱ ላገልግሎት ሊያመለክቱ ሲሄዱ ይገልጽልዎታል:: በድርጂቶቹ የሚሰጡ አገልግሎቶች ለተወሰኑት እስከ አምስት ዓመት ሊቆዩ ይችላሉ::

**ለሌሎች ተጨማሪ አገልግሎቶች ተጠቃሚ መሆን ይቻላል?**

ወደ ማህበራዊ አገልግሎት ተቋሞች ለስደተኛ ማቋቋሚያ አገልግሎትና ድጋፍ ሊያመለክቱ ሲሄዱ ሌሎች ተጨማሪ አገልግሎቶች መኖራቸው በመጠየቅ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይቻላሉ::